## ጋዜጣዊ መግለጫ

## <u>የኢትዮጵያ ኮሙኒኬሽን ባለሥልጣን ለሁለት የቴሌኮሙኒኬሽን ፈቃዶች አስራ ሁለት የፍላጎት መግለጫዎችን ተቀበለ፡፡</u>

**ሰኔ 26 ቀን 2012፣ አዲስ አበባ**

የገንዘብ ሚኒስቴር እና የኢትዮጵያ ኮሙኒኬሽን ባለሥልጣን (ኢኮባ) ሁለት አዲስ የቴሌኮሙኒኬሽን ፈቃዶችን ለመስጠት ግንቦት 13 ቀን 2012 የፍላጎት መግለጫ ሂደት ይፋ አድርገዋል፡፡

ተጫራቾች የተጠየቁትን መረጃዎች በማቅረብ ፍላጎታቸውን እንዲገልጹ የአንድ ወር ጊዜ ተሰጥቷቸዋል፡፡ ተጫራቾች በፍላጎት መግለጫው ውስጥ ተቋማዊ አደረጃጀታቸውን፣ በአለም አቀፍ ደረጃ ያላቸውን ሽፋን፣ አገልግሎት የሚሰጡባቸውን ሀገራት ዝርዝር፣ ያላቸውን የሞባይል ደንበኞች ብዛት እንዲሁም የተጫራቾችን አቅም ለመገምገም እና የብቃት መስፈርቱን በበቂ ሁኔታ በመለየት ለኢትዮጵያ የቴሌኮሙኒኬሽን ገበያ በጣም ተስማሚ የሆኑ ኦፕሬተሮችን ለመምረጥ ሊረዱ የሚችሉ ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን እንዲያቀርቡ ተጠይቀዋል ፡፡

በዚህ መሠረት በፍላጎት ማቅረቢያው መዝጊያ ቀን ማለትም ሰኔ 15 ቀን 2012 የኢትዮጵያ ኮሙኒኬሽን ባለሥልጣን 12 የፍላጎት መግለጫዎችን የተቀበለ ሲሆን ከእነዚህም ውስጥ 9ኙ ከቴሌኮም ኦፕሬተሮች እና 2ቱ የቴሌኮም ኦፕሬተሮች ካልሆኑ እንዲሁም አንዱ (1) ተሟልቶ ያልቀረበ ናቸው፡፡ የኢትዮጵያ ኮሙኒኬሽን ባለሥልጣን **“ዓለምአቀፍ ትብብር ለኢትዮጵያ” በሚል ጥምረት ቮዳፎን፣ ቮዳኮም እና ሳፋሪኮም በአንድ ላይ፣ ኢቲሳላት፣ አክሲያን፣ ኤምቲኤን፣ ኦሬንጅ፣ ሳውዲ ቴሌኮም ኩባንያ፣ ቴሌኮም ደቡብ አፍሪካ፣ ሊኪውድ ቴሌኮም፣ ስኔይል ሞባይል** እና ሌሎች ሁለት ቴሌኮም ኦፕሬተር ያልሆኑ **ካንዱ አለምአቀፍ ቴሌኮሙኒኬሽን** እና **ኤሌክትሮሜካ አለምአቀፍ ፕሮጀክቶች** የተሟላ መረጃ እና የፍላጎት መግለጫ መቀበሉን ያረጋግጣል፡፡

የገንዘብ ሚኒስቴር እና የኢትዮጵያ ኮሙኒኬሽን ባለሥልጣን ለፍላጎት መግለጫ ጥያቄው ምላሽ ለሰጡና ፍላጎታቸውን ለገለጹ ተጫራቾች በሙሉ ምስጋናችንን እናቀርባለን፡፡ የኢትዮጵያ ኮሙኒኬሽን ባለሥልጣን ለቀጣዩ ምዕራፍ የሚያደርገውን ዝግጅት ተሳታፊዎቹ እንዲገነዘቡ እና እንዲሳተፉ ያደርጋል፡፡ የቴሌኮሙኒኬሽን ዘርፍ ማሻሻያውን ለማሳካት እና የዲጂታል ሽግግሩን ለማሳለጥም የኢትዮጵያ ኮሙኒኬሽን ባለሥልጣን የጸና አቋም ያለው መሆኑን ያስታውቃል፡፡

<u>አድራሻ</u>

የኢትዮጵያ ኮሙኒኬሽን ባለሥልጣን፣ ኢ-ሜይል: contact@eca-ethiopia.com

ስልክ: +251 11 465 6011